# መስመር የሳተው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ወደ መስመሩ ይግባ!

ዘነበ በቀለ

የኢትዮጵያ ሙዚቃ መንታ መንገድ ላይ ቆሞ እየተቸገረ ነው። ኪነጥበብ የምትፈቅደውን እውነት ገልፆ ከህዝብ ወግኖና ሀቅን ተናግሮ ከመሸበት ማደር አሊያም የሀሰት ክበሮን እየነረቱ ሰሚን ማደናበር ነው ምርጫው። በዚህ መልኩ የተካኑ ሰዎች ተሰግስገው እንደገቡ አሌ አይባልም። ነገ ጠዋት ሀፍረቱን ለኪነት አክናንበው ዶቃቸውን ለቅመው እንደሚሰወሩም የታወቀ ነው። ውርደቱና ሀፍረቱ የሚቀረው ግን ለኪነጥበብና ለኪነት ሰዎች ብቻ ይሆናል። ስለዚህም ከመስመር ወጥቶ የሚንዘውን ቶሽ ማለት የሙያው ሰዎች ሀላፊነት ይሆናል። መጀመሪያ ደርግ የሙዚቃ ትምህርትንና ተቋሞቻቸውን እየዘጋ ሙያውን ወደ ቀበሌ በማስተላለፉና በዚያ ሁኔታም የሰለጠነው ሙያተኛ በየበዓላቱ ላይ ተሳታፊ በመሆን በቀበሌ ካድሬዎች እጅ ተመርቆ ሙዚቀኛ የሚል ቅፅል እንደተለጠፈበት ግልፅ ነው። ሙዚቀኛ ማለት አንጎራጓሪ ዘፋኝ እንደሆነ ተደርጎም በመታየቱ የሙያው ትምህርታዊ ስልጠና አላስፈላጊ ነው ተብሎ የተደመደመ ይመስላል። በመሆኑም አሁን እንደሚታየው ሙዚቃን በስርዐት አጥንቶ ከሚያቀርበው ይልቅ በራሱ ጥረት መሳሪያዎችን ተጫውቶ አሊያም አንጎራጉሮ ነጠላ ዜማ ለቃቂው ሶልዲቷን ሲለቅም በመታየቱ የሙዚቃ አፍቃሪ ወጣት ከትምህርቱ ይልቅ ወደ ልምዱ ማመዘኑ እየታየ ነው። ወያኔ "የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጪው" የሚል በመሆኑ ማንኛውም ነገር ሶልዲ መሰብሰቢያ እስከሆነ ድረስ ጥቅም አለው ብሎ ያምናል። ስለዚህም ነጠላ መልቀቁ ድርብ መጨፈሩ ለወያኔ አዝዝ ተስፋ አመላካች ድርጊት ነው። ለሀገር ለባህል ግን ውድቀትን መጋበዙ ጥርጥር የለውም። ህዝብ ዘለዓለሙን ከሀገር ባህልና ከጎሳ አመላካች ሙዚቃ አቀራረብ እንዳይወጣና፣ ኪነታዊ ጥበብን ሳይሆን ቋንቋዊ ትርጉምን ሲያደንቅ እንዲኖር የሚፈቅዱት ህዝብ ህሊናዊ ግንዛቤን ትቶ ስሜታዊ ቅስቀሳንና / ኩርኩራን ሙጥኝ ብሎ እንዲይዝ ለዚህ ዓላማም እንዲመቻች የሚገፋፉት አምባገነን ገዥዎች ናቸው።

ሰሞኑን እየተናፈሰ ያለው የሸራቶን ሆቴል ኮንሰርት አለመሳካት በዚሁ መንገድ የተገፋ መሆኑን ያመለክታል። በካድሬዎች አፍ ብኩርናቸውን ለማፀደቅ ደፋ ቀና ያሉት ዘመናዊ ዘፋኞች እየተመረጡ ወደ ሸራቶን ሲላኩ ለሙያው እድገት ታስቦ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። የሚያሳዝነው የሙያውን ኤቲክስ ስተው በአቋራጭ ለመክበር የሚራወጡት ባለሙያዎች "ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም" የሚለውን ያባቶች ብሂል የዘነጉ መሆናቸው ነው።

1ኛ) በድምፅ አሰለጣጠን - የኢትዮጵያ ሙዚቃ አደገ በተባለበት በ60ዎቹ ውስጥ እንኳ ለድምፅ ስልጠና ብዙ ትኩረት ተሰጥቶት አያውቅም። ያሬድ ት.ቤት ወደ አዲሱ ህንፃ ከመዛወሩ በፊት በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳለ ሁለት በድምፅ የሰለጠኑ አፍሪካ አሜሪካዊ መምህራን ነበሩት። ሚስ ዊክስ እና ሚስተር ቬጋ የሚባሉ የተለያዩ መዝሙሮችን የሚያስጠኑ ነበሩ። ሚስተር ቬጋ በተለይ ከድምፅ መምህርነቱ ይልቅ የነሀስ መሳሪያዎች / ትራምፔት አስተማሪ ሆኖ ይሰራ እንደነበር አስታውሳለሁ። ስለዚህም ያሬድ ሲጀመር ለድምፅ ጥናት መደበኛ የሆነ ክፍል አልነበረውም። ድምፅን ለማጥናት በሚስተር ነርሲስ ናልባንዲያን የህብረ ድምፅ ጥናት ውስጥ ነበር የምንካፈለው። በሁዋላ ላይ ተጀምሮ እንደሆን አላውቅም። ምክንያቱም እንዲት አስቴር ዲባባ የምትባል የድምፅ ትምህርት ባለሙያ ጓደኛችን ከውጭ ስትመለስ የድምፅ አስተማሪ ሆና ነበር የሚል ሰምቻለሁ። እሷን ብቻ ነው በሙያው የሰለጠነ ሰው የማውቀው። በተቀረ ግን በርካታ ዘፋኞችን ማፍራት የቻሉት ልዩ ልዩ የወታደር ክፍሎች እና መንግስታዊ

የሆኑ ተቋሞች ናቸው። ሁሉም የሙዚቃ ተቋሞች በሚፈልጉት የሙዚቃ ስታይል እንዲሰማሩ የሚያደርጓቸው ሰዎች የዘፈን ችሎታ አለን ብለው ለመቀጠር ወደነሱ ዘንድ የሚመጡትን ነው። የአርቲስቶቻቸው ደረጃ እንዲሻሻልና የድምፅ ገደባቸውም አስተማማኝና የረጋ እንዲሆን በተቻለ መጠንም ከፍ ያለ ሬንጅ እንዲኖረው ለማድረግ በፒያኖ እየተረዱ ስለሚያለማምዱ ብዙዎቹ መሰረታዊ የሆነ የድምፅ ማውጣት ጥበብን ያውቃሉ። ቢያንስ የጉረሮ የራስ፣ የትናጋና የደረት ድምፆችን የአሰራር ስልት ስኬሎቹን በሚለማመዱበት ጊዜ መገንዘብ ይችሉ ነበር። ከዚህ ሌላም ወደተግባር በሚሰማሩበት ወቅት ለድጋፍ ያህል የሚሰጡትን የመሳሪያዎች ኢንተርሉድስ በሚገባ አጥንተው የራሳቸው አስተዋፅኦ በሙዚቃው ውስጥ ምን ሊመስል እንደሚችል ጠንቅቀው የሚረዱበትን ሁኔታ ይፈጥርላቸው ነበር። በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ የሚታዩ ቅላጼዎች የጊዜ ተመንና የኢንተርቫል አይነቶች ያሏቸው በመሆኑ የት ላይ መቀለፅ እንደሚያስፈልግ ማወቅ ተገቢና አስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ዘፋኙ መቀለፅ የሚያስፈልገው በየትኛው ቶን ላይ እንደሆነ መረዳት ያሻል ማለት ነው። አላስፈላጊ ቅላጼዎችን መጨመር የዜማውን ባህርይ ያዛባል። በትዝታ ሙዚቃ ላይ የሚደረግ ቅላጼ በአምባሰል ዜማ ላይ እንዲሁም በሌሎቹ ስልቶች በተመሳሳይ ደረጃ ላይ መዋል አያስፈልገውም። ዶሚናንት እና ቶኒክ ድምፆች የድምፅ ማረፊያ ስሜት ስላላቸው በቅላጼ ቢወጠሩ አጠቃላዩን የዜማ ስልት ኢትዮጵያዊ ስሜት እንዳይዝ ሊያደርገው ይችላል። በኢትዮጰያ ሙዚቃ ውስጥ /ድፋት/ የዜማ ማኖሪያ ማሳረፊያ በመሆኑ በቅላጼ አይታጀብም። አለበለዚያ እንደ አረብኛ ሙዚቃ መዝጊያው እንዲራዘም ያደርጋል።

2ኛ) የመሳሪያ አጀብ መስጠት

የኢትዮጵያ ሙዚቃ ጠባዩ እርስ በእርስ በመደጋገፍ በመቀባበል የሚሰራ በመሆኑና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የባህል ሙዚቃው ነፀብራቅ በመሆኑ ሶሻል ዩኒሰን፣ ኢቲሬቲቭ፣ ሆኬት ፎርም፣በአብዛኛውም ኢሚቴሽናል ሪስፖንስ፣ እንዲሁም አንቲፎናል (ሁለት ግሩፖች በጠሪና ምላሽ) መልክ የሚጫወቱት አይነትን ያቀፈ ነው። የኢትዮጵያ ሙዚቃ እላይ እንዳልኩት ጠባዩ የሚደጋገፍና በኢንተርሉድና ፕሬሉድ ቴክኒክ የሚሰራ እንጂ እንደ ሩቅ ምስራቅ ወይም እንደ መካከለኛ ምስራቅ በአጃቢነት በመሳሪያዎች /ቦርዶን/ ድምፅ  አይገለገልም። የቴክኒዎሎጂው ውጤት የሆነው ዘመናዊው የሲንቲሳይዘር ሙዚቃ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ይስታል። አንደኛው የብዙ ተጫዋቾች መነሻ የባህል ሙዚቃ በመሆኑ ባህላዊው ሙዚቃ ፈሩን እንዲያጣ ያረገዋል። ሁለተኛው የመሳሪያዎቹ  አመራረጥ ዜማዊ ቀለሙን የሚከተል ባለመሆኑ እና አንዳንዶቹ ለተወሰኑ ባህሎች መገለጫ የሚውሉ በመሆናቸው ቢደነቀሩ ሀገራዊ ጣዕሙን ያጠፉታል። ለምሳሌ "ሻሚሶን" ባለ ሶስት ክር መሰንቆ መሳይና "ሻኩሀቺን" አጭር የጃፓን ዋሽንት ወይም የቱርክን ካኑን ከ17 እስከ 25 የሚደርስ እንደ አውሮፓውያኑ "ሉቶርና" መሳሪያ የሚመስለው በአጠቃላይ የሩቅ ምስራቅም ሆነ የመካከለኛው ምስራቅ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአጃቢነት ሲገቡ ኢትዮጵያዊውን የክራርና የመሰንቆ ወይም አራት ቀዳዳ ድምፅ ዋሽንትን ልዩ ጠባይ ተጋፍተው ነውና የሚወጡት የሙዚቃ ስልቶቹን/ቅኝቶቹን ለዛ የመቀየር ሀይል ይኖራቸዋል። በመሆኑም አቅራቢዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ይጠበቅባቸዋል። በዘመናዊ ቴክኒዎሎጂ የሚታገዘው የድምፅ አዘማመር ዘዴም ያላግባብና ያለቦታው ቅላጼ ከጨመረ ሀገራዊ የሆነውን የዜማ ቃና መቀየሩ የማይቀር ነው።

በሌላ በኩል ግን ሲንቲሳይዘሩ እንደ ቀድሞው ዘፋኙን ለከፋ ችግር የማይዳርግ ሁኔታ ይፈጥራል። ሲንቲሳይዘሩ የዘፋኙን የድምፅ ገደብ ጠብቆ በተፈለገው ስኬል አይነት የመጫወት አቅሙ ከፍተኛ በመሆኑ ዘፋኙ የራሱን የድምፅ እርከን አውቆና ተዝናንቶ ለማቅረብ የሚያስችለው ሁኔታ ይፈጥርለታል። የተለያዩ ያጨዋወት ዘዴዎችንም ለመምረጥ ያግዘዋል። በዚህ በኩል በቀድሞው አሰራር አኩስቲክ/ አፕላይድ ሙዚቃን/ ለማቅረብ የእያንዳንዱን የመሳሪያ ባህርይና የድምፅ ቀለም ለይቶ ማወቅ ግዴታ ነው። ምናልባትም መሳሪያዎቹ ባለባቸው ችግር ምክንያት ማለትም የ ሲ ሻርፕ ወይም ተመሳሳይ ከፍተኛ ቁልፍ ያላቸውን ስኬሎች ለመጫወት ብዙዎቹ መሳሪያዎች ለምሳሌም እንደክላሬኔት ያሉ ችግር ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ ስላለ መሳሪያዎቹን ወደ ዝቅተኛ ቁልፍ ወዳላቸው ስኬሎች ማውረድ ስለሚያስፈልግ፣ አቀናባሪው መለኛ ካልሆነ፣ በቀር ዘፋኙ ያላቅሙ ድምፅ እንዲያወጣ ሊያስገድደው ይችላል። ብዙውን ጊዜ ዘፋኞቹ ሲጮሁ የሚደመጡት በዚህ ያልተመጣጠነ የድምፅ ገደብ ቅንብር የተነሳ ነው። ይህ አይነቱን ሽግግር እንደ ኮሎኔል ሳህሌ ደጋጎ አይነቶቹ አቀናባሪዎች በአስገራሚ ቴክኒክ ያልፉት ነበር።

አንዳንድ ጊዜ የሙዚቃዎቹን አይነትና የሚከተሉትን ስልት ጠንቅቀን ለመረዳት ባለመቻላችን፣ የአሸናፊ ከበደን ከሙላቱ አስታጥቄ ሙዚቃዎች ጋር ለማነፃፀር ይከጅለናል። ስናወዳድር ሁሉንም በሁሉም ዘርፍ አይደለም። አንዱን በሁሉም ዘርፍ እንጂ!! ይህ አይነቱ አፈራረጅ ስህተት ነው። ምንም እንኳ ጥላሁን ገሰሰ ሁለገብ አርቲስት ቢሆንም፣ ዓለማየሁ እሸቴ ለሮክንሮል ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ መሆኑ መታወቅ አለበት። ከሱ በፊት በዚህ ሙያ ላይ ፋና ወጊ የነበረው ተስፋዬ ገብሬ "የፍቅር ምግብ" በሚለው ሙዚቃው ታዋቂ እንደ ነበር ይታወሳል። ሙሉቀን መለሰ በሪዝም-ኤንድ-ብሉስ አጨዋወቱ ተወዳጅና ተደናቂ መሆኑ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ላይ ያከለው ኢምፕሮቫይዜሽናል ቴክኒክ የማይናቅ ነው። መሃሙድ አህመድ ለኦፔሬታ አዘማመር ስልት የሰጠ ድምፅ እንዳለውና እስካሁን ምትክ የሌለው መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል። ሌሎችም በየራሳቸው ስልት ሁሉም የየራሳቸው ውበት ስላላቸው መዳኘት የሚኖርባቸው በዚያው መልክ ነው። ለምሳሌ አስቴር አወቀ የእንጉርጉሮንና የዘፈንን ስታይል ደባልቃ በማቅረብ የመጀመሪያዋ ናት። በአንድ ወጥ የዜማ ሂደት በቶሎ ሊጠና የማይችል ባለብዙ ፎርም ምናልባትም a b a c ወዘተ. ፎርሞችን ባህርይ የሚያሳይ ዜማ በማቅረብ አስቴር ንዋይ ደበበና መልካሙ ተበጀ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። በአጠቃላይ በበፊቱ ዘመን አንዱ ሌላውን ለመምሰል ሲቸገር አይስተዋልም። እራሱን መምሰሉ ይበልጥ ዋጋ ያለው ነገር መሆኑን በመቀበሉ በመድረክ ላይ ወጥቶ ዝግጅቱን ሲያቀርብ ና! ውረድ የተባለ ከያኒ አላውቅም። ምክንያቱም በስርዓት ተዘጋጅቶ ተጨንቆና ተጠቦ የሚቀርብ ድምፃዊ እንጂ ተመልካችን የሚደፍርና ላም ባልዋለበት ኩበት የሚለቅም ባለመሆኑ ነው።

ወጣት ከያኒያን አንድ ያወጡት ሀቅ አለ። ይህም የኢትዮጵያ ሙዚቃ ስኬልም ሆነ የሙዚቃ ፎርሙ ተመሳሳይና በይበልጥም በባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ ውህደቱ በጉልህ የሚታይ መሆኑን በተግባር ማስመስከር ነው። ይህ ክፍል ባለፉት ዘመናት እምብዛም ትኩረት የተሰጠው አልነበረም። የኢትዮጵያ ሙዚቃ ስንል የሰሚኑ ሜሎዲ ከደቡብ ሪትም ጋር ተዋህዶ የፈጠረው መሆኑ የታወቀ ነው። የወላይታ ሙዚቃ ምትና የአማርኛ ግጥም፡ የትግሪኛ ሙዚቃ ምትና የአማርኛ ግጥም፣ የኦሮምኛ ሙዚቃ ምትና የአማርኛ ግጥም። የሀመር ሙዚቃ ምትና የአማርኛ ግጥም አብረው ሲሰሩ አንዳችም የሙዚቃ ህግ ፍልሰት ያላሳዩበት ምክንያት በሞድ በፎርም እና በስታይል የተዋዋጡ በመሆናቸው ነው። ከዚህ ሌላም የአማርኛ የግጥም ስልት ያለምንም ችግር ከሌሎቹ ቋንቋዎች ጎን ለጎን መሰለፍ መቻሉ በራሱ የቋንቋውን ብሄራዊነት ብቃት ያረጋግጣል።

በ ኢ.ዶል ፕሮግራም ላይ እንዳስተዋልኩት፣ በዳኝነት የሚያገለግሉትን ወጣት የሙያው ሰዎች በሚያሳዩት ሙያዊ ብቃት የማደንቅና የምኮራባቸው ቢሆንም፣ አሁንም ፕሮግራሙ የሚቀረው ነገር አለና እንዲስተካከል መጣር ይኖርባቸዋል እላለሁ። ይኸ ኢ.ዶል የተሰኘ ሌላውን የመምሰል አባዜ የተጠነሰሰው ከፈረንጆቹ ፖለቲከኞች ጎራ ነው። ህፃናት በጨቅላ አንጎላቸው የሰጧቸውን ብቻ ተቀባይ እንዲሆኑና መልሰውም እንደ በቀቀን ያሏቸውን እንዲያስተጋቡ ለማድረግና፣ የፈጠራ ክህሎትን ለማኮስመን ብዙሀኑ በማስመሰል ጥበብ የተካኑ የጥቂት ፈጣሪዎች አድናቂና ተከታይ አድርጎ ለማስቀረት በዓለም ደረጃ የተሰላ ጎርባጣ የፖለቲካ መንገድ ነው። በተፋጠነ መልኩ የተዛመተውም ለዚሁ ዓላማ ሲባል የተወጠነ በመሆኑም ጭምር ነው። ይሁን እንጂ! ቀደም ብለው የተከታተሉት ሀገራት ህዝቦች ጥቅምና ጉዳቱን አመዛዝነውና ሰልችቷቸው እርግፍ አድርገው ትተውታል። አሁን እንደብርቅ ሆኖ የሚታየው ሁዋላ ቀር ናቸው በሚባሉት ሀገሮች ውስጥ ነው። አስቀድሞም የታቀደው ለነሱ በመሆኑ ልክ እንደ ኤድስ በሽታ ግቡን መቷል። ሀገራችን የምትታወቀው እንዳለ በመገልበጥ ሳይሆን ፍሬ ሀሳቡን በመተርጎም ነውና ይህንንም ገልብጠን በራሳችን መንገድ መጠቀሙ አግባብ ነው። ባህላዊው ኪነጥበብ ፈር እንዳይለቅ ማድረግ ከሙያው ሰዎች የሚጠበቅ ግዴታ ነው። ሙዚቃን ምናልባት ከድራማ ጋር የሚለየው አንዱና ዋና ነው የምለው፣ ድራማ ባህርያትን አጥንቶ ሳይጨምር ሳይቀንስ እንዳለ መልሶ የሚያቀርቡበት ጥበብ ሲሆን፣ ሙዚቃ ግን ክስተቱን ቀስሞና ተገንዝቦ በራሱ ስሜትና ኦርጂናሌ ስራ መተርጎም ነው።

በዚህ በኩል ስመለከተው የ ኢ.ዶል አዘጋጆች ባህላዊውንም ሆነ ዘመናዊውን እየደባለቁ ማቅረባቸው ምናልባት የፕሮግራሙን ዕድሜ ለማራዘም ይረዳ እንደሁ እንጂ ትምህርታዊ ፋይዳ ያለው መስሎ አይታየኝም። ምክንያቱም ራሳቸውም ለዳኝነት ስለሚቸገሩ ለሙያው ብቃት የሌላቸውን ሰዎች ተመሳሳይ ቋንቋ በመናገራቸውና የአካባቢው ሰው በመሆናቸው ብቻ ፍርድ እንዲሰጡ ሊያደርጉ ነው ማለት ነው። አለያም ተመልካቹን ምን ታስባላችሁ "ይመጥናል?" እያሉ ለመጠየቅ ይገደዳሉ። የሙዚቃ ውድድሩ በዘፋኝነት ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፣ የድምፅን ትምህርታዊ ዕድገት ይገታል የሚል እምነት አለኝ። በእርግጥ የፕሮግራሙ መሪዎች በተደጋጋሚ ሙያተኛ ሰው ፈልገህ ምክርና ዕርዳታ አግኝ! እያሉ መናገራቸው የሚያስደስት ነው። ነገር ግን እንደተመለከትኩት ዋናው መለኪያ የዜማ ቅላፄ ማበጀት ነው። ቅላፄ ደግሞ በራሱ የድምፅ መለኪያ የመሆን ብቃቱ እንደ ባህሉ ይለያያል። በደቡብ ኢትዮጵያ ያለው የዶርዜ ፎር ፓርት ካኖን የጊዶሊ ኮሎቶሚክ የዜማ ጠባይ አንዱ ባንዱ ላይ ታኮ በአጋዥነት የሚወጣ ድምፅ በመሆኑ የቅላፄ ባህርይ ለመጨመር ያውካል። ስለዚህም ለማወዳደር አይመችም ማለት ነው። በአጠቃላይ የባህል ሙዚቃዎችን ለዘመኑ ለትውልዱና ለአካባቢው ትቶ ትምህርታዊ ውድድሩን በዘመናዊ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ማድረግ ጥሩ ይመስለኛል። በዚህ በኩል ተወዳዳሪው የሌላ ሰው ዘፈን እንኳ ቢጠቀም የራሱን ኢምፕሮቫይዜሽን አክሎ ማቅረብ ያለበት መሆኑ ይበልጥ ችሎታውን ሊያሳይ ስለሚችል ለውድድር ብቃትን ያረጋግጣል። ሌላውን ለመምሰል ከመጨነቅም ያድናል።

ሌላው ደግሞ የፕሮግራሙ መሪዎች በሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች መሃል ያለውን ችሎታ ለማዳበር ለተጫዋቾቹ ዕድል ቢሰጡ ይበልጥ ይጠቅማል እላለሁ። ለመሆኑ ምን ያህሉ ሰው ምን አይነት መሳሪያ እንደሚጫወት ይታወቃል! ዕድሉ ቢሰጥ ጊታርና ሲንቲሳይዘር ተጫዋቹ ግልብጥ ብሎ ሳይመጣ የሚቀር አይመስለኝም። ያ! እንግዲህ ስቴት ኦርኬስትራ የመመስረት አቅማችንን ያሳያል ማለት ነው። የትሮምቦንና የትራምፔት ተጫዋች ለምልክትም ሲጠፋ ወይም ሲመነምን ማየት ሙዚቃ ዕድገቱን ጠብቆ እየተጓዘ ነው ያሰኝ ይሆን? እነ ፍሬንች ሆርን፣ እነ ኢንግሊሽ ሆርን፣ እነ ባሱን፣ እነ ኦቦ፣ እነ ፍሉትማ ተከድነው ይሻግቱ ተብሎ ሳይፈረድባቸው አይቀርም። እናም የኢዶል አዘጋጆች ፕሮግራማቸውን በማስተካከል፣ በተለያዩ የሙዚቃ ዘርፎች ትምህርታዊ ገለፃቸውን እያጎለብቱ ቢቀጥሉ ከፍተኛ አስተዋፃኦ አለው ብዬ አምናለሁ።

ድምፃዊያኑን በተመለከተ ግን ጥሩ ደረጃ ላይ ያሉ ነው የሚመስለኝ። የድምፅ ደረጃቸውን ተከትሎ የሚሰራላቸው መሳሪያ ስላገኙ ሊሆን ይችላል። በድምፅ በኩል ከድሮው በበለጠ የድምፅ ገደባቸውን አውቀው የሚጫወቱ በርካታ ዘፋኞች የተገኙት አሁን ነው እላለሁ። ስለ ድምፅ አወጣጥ ብዙ ጭንቀት ያለባቸው አይመስልም። ችግሩ የሚከሰተው ከተለማመዱበት ሜጀር/ማይነር ስኬል ወጣ ሲል ሊሆን ይችላል። በሸራተን ተከሰተ የተባለው የኮንሰርት አለመሳካትም ከዚህ ጋር የሚያያዝ ይመስለኛል። በተረፈ የፕሮግራሙ አቅራቢዎች የሙያው ተጠሪዎች ናችሁና በርቱ! ቀጥሉበት! የፕሮግራሙን ስም ግን በኢትዮጵያዊኛ ለውጡት!

ኢትዮጲያ ለዘለዓለም ትኑር!!